# ኢትዮጵያችን

*የአንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ (ኢትዮጵያችን) ልሳን*

ኢትዮጵያችን ቅጽ 2 ልዩ ዕትም ቁጥር 3 የካቲት ፳፱ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.


## ማርች 8ን ስንዘክር

**(ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን (ማርች 8) 107ኛ ዓመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ)**

ሴቶች በእማዊ ዘመን የነበራቸውን የወሳኝነት ሚናና ስልጣን ቢነጠቁም ዛሬም ብልህነት የተሞላበት ሀሳብ ባለቤት በመሆናቸው ዓለም ለደረሰችበት የስልጣኔ ደረጃ ዋና አንቀሳቃሽ ሞተር ሆነው ቀጥለዋል። ጎልቶ አይዘመርላቸው እንጂ ዛሬም ሴቶች በተለያዩ መስኮች ያላቸውን ብቃት በተግባር እያሳዩ ይገኛሉ። ከትንሹ የቤተሰብ አስተዳደር ጀምሮ ትላልቅ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ የሆኑ መልካም ውጤቶች ሁሉ ያለ ሴቶች ተሳትፎ አልተሳካም።

በእማዊ ዘመን እናቶች የበላይ አስተዳዳሪ ነበሩ። የእማዊ ዘመን ተቀይሮ በማህበራዊ ኑሮው የነበራቸው የበላይነትና ስልጣን እየተሻረ ሲመጣ ሴቶች ለመውለድና ልጅ ለማሳደግ ብቻ የተፈጠሩ ሆነው ተቆጠሩ። በኢኮኖሚው የወንድ ጥገኛ ሆነው በቤት ውስጥ ስራ ብቻ መዋል ጀመሩ። የኢኮኖሚ ጥገኛ መሆናቸው ደግሞ በማህበራዊና በፖለቲካው የነበራቸው ተቀባይነት እየቀነሰ በቤትም በአደባባይም የነበራቸውን ጉልህ ሚና አሳጣቸው። በዚህም ምክንያት የወሳኝነታቸውን ደረጃ ተነጥቀው ዝቅ ተደረገ። ድርብ ድርብርብ ጭቆናም ይደርስባቸው ጀመር። እያደርም የየሀገራቱ ወግ፣ ልማድና ባህል የሴቶች የበታችነትን አጉልተው የሚያሳዩና ሴቶችን በሴትነታቸው የሚያሸማቅቁ ሆኑ። የሃይማኖት መሪዎች ሳይቀሩ ሴቶች ለወንዶች ጸጥ ለጥ ብለው እንዲገዙ የሚሰብኩ ሆኑ። ሴቶች በሴትነታቸው ዝቅ ተደርገው በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካ ተሳፎአቸው የሚደርስባቸው አድሎና የወንድ የበላይነት በጋራ ተጠራርተው መታገል እንዳለባቸው ተገነዘቡ። ይህ የወንድ የበላይነትና ጭቆናን ለማስወገድና ለመቋቋም ብሎም መብታቸውን ለማስከበር የዓለም ሴቶች መጠራራትና አንድ ላይ መቆም ግድ ሆነና ማርች 8 (የካቲት 29)ን ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ወለደ። ሴቶች መብታቸው ተከብሮ ጥንካሬያቸው ለመላው ዓለም ይታወቅ ዘንድ የዛሬ 107 ዓመት እ.ኤ.አ በ1911 በአንድ ላይ በመቆም በጀርመን፣ በአውስትሪያ፣ በዴንማርክና በስዊዘርላንድ ድምጻቸውን አሰሙ።

የኢትዮጵያ ሴቶች በየዘመኑ የአኩሪ ገድል ባለቤት ቢሆኑም እንደ ሌላው ዓለም ሴት እህቶቻቸው ሁሉ ሴቶችን ዝቅ አድርጎ በሚያይ ማህበረሰብ ውስጥ በመኖራቸው ታሪካቸው ተፈላጊውን ያህል ሳይጻፍና ተገቢውን ቦታ ሳያገኝ ተድበስብሶ ቀርቷል። የኢትዮጵያ ሴቶች የሌላው ዓለም ሴቶች አካል እንደመሆናቸው መጠን የጾታ አድሎና ከወንድ እኩል አለመታየታቸው ዛሬም ቢሆን በሰፊው የሚታይ ሀቅ ሆኖ ዘልቋል። የኢትዮጵያ ሴቶች የጾታ ጭቆናና አድሎን ለመታገል ከዓለም አቀፍ የጾታ አጋሮቻቸው ጋር ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ ትግሉን ተቀላቅለው አብረው ጩኸታቸውን ማሰማት ጀምረዋል።

***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** ለ107ኛው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 ክብረ በዓል የኢትዮጵያ እናቶችን፣ ወጣት እህቶቻችንን እንዲሁም ታዳጊ ሕፃናትን በጥቅሉ የኢትዮጵያ ሴቶችን እንኳን አደረሰን/አደረሳችሁ እንላለን። ***"ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** የሴቶችን

ትግልና እንቅስቃሴ በአጽንዖት ይከታተላል። ያለ ሴቶች ተሳትፎም ትግል ሁሉ ተፈላጊውን ግብ እንደማይመታ በመገንዘብ ***"ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** ሴቶች ከጎናችን በመሆን የትግሉ አንቀሳቃሽ ሞተር ይሆኑ ዘንድ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል አብሮም ይታገላል።

***"ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** ከተነሳንበት አንዱ ዓላማ የወደፊቷን ኢትዮጵያ የአዲሱ ትውልድ ወጣቶችና ሴቶች ይረከቡ ዘንድ መሥራት ነው። *ኢትዮጵያ ሀገራችን ዳር ድንበሯን አስጠብቃ፣ የሕዝቧን አንድነት ቀዳሚ አድርጋ፣ መለያ ሰንደቅ ዓላማዋን ከፍ አድርጋ ለዘላለም ትኖር ዘንድ ከፍተኛው ኃላፊነት ያለው በአሁኑ ትውልድ ወጣቶችና ሴቶች እህቶቻችን ላይ መሆኑን እናሰምርበታለን።* በአሁኑ ወቅት በተያያዘው ሕዝባዊ ትግል የሴቶች ተሳትፎ ቀላል እንዳልሆነ ብንገነዘብም በተጠናከረና በተደራጀ መልኩ መታገሉ ደግሞ ጠቀሜታው የጎላ ነው እንላለን። በመሆኑም ትግሉ አስፈላጊውን ግብ ይመታ ዘንድ፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ በወያኔ/ህወሓት መቃብር ላይ ታብብ ዘንድ ሴቶች በትግሉ ተደራጅተው ግዳጃቸውን እንዲወጡ ***"ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** የድርሻችንን እንደምናበረክት ጥሪ እናቀርብላችኋለን።

ሴቶቻችን የትግሉ ቆስቋሽ ሞተር ናችሁና ተሳትፎአችሁን አጠናክራችሁ ሕዝባዊ ትግሉን ከግብ አድርሱት እንላለን። አስተዋይነታችሁና ብልህ አመራራችሁ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ይፈለጋል እንላለን። "ምግብ ያለ ጨው. . ." እንዲሉ ትግል ያለ ሴቶች ተሳትፎ ግቡን አይመታም። የህብረተሰቡ ግማሽ ኃይል እህታችን "እንዲያው ዘራፌ የዋ…፤ እንዲያው ዘራፌ ዋ…" ያላለችበት ትግል ጨዋታ ነው። በትግሉ ዓውደ ሜዳ ላይ እመህል ገብታ "በ ለ ው፤ በ ለ ው፤ በ ለ ው" ብላ ድምቀትን ስትሰጠው ድሉም ይቃረባል። በዛሬው ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 ለሴቶች እህቶቻችን ጥሪያችን ከትግሉ ጫፍ ብቅ በሉ ነው።

የ***"ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** አባላት ማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶችን ቀን ስናስብ በተለይ የኢትዮጵያ እናቶችን ሁኔታ ስንዘክር በመጀመርያ ዐይናችን ሥር ድቅን የሚለው መብታቸው መረገጡ ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያውያን ሴት እናቶቻችንና እህቶቻችን የኢኮኖሚ ጥገኛ መሆናቸው ብቻ አይደለም የሚያስጨንቀን። የኢትዮጵያ እናቶችና እህቶችን ስናስብ አእምሮአችንን የሚያደማው ከወንዶች እኩል አለመታየታቸው ብቻ አይደለም። ከ80 በመቶ በላይ በሆነው የገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖሩ ሴቶች ቀኑን ሙሉ አሰልችና አናዋሽ በሆነው የማጀት ውስጥ ሥራ ሲባክኑ መዋላቸው ብቻ አይደልም በደላቸው። የኢትዮጵያን ሴቶች ለ50 ዓመታት ያልህ መከራና ሰቆቃ የተላበሰች፣ ያላረፈች፣ የተሰቃየች፣ ተሸሸግበት፣ ትደበቅበት ጥግ ያጣች እፎይ ያላለች ሕይወታቸው ናት ልባችንን የምታደማው። ይልቁንስ የሚታሰበን ለ50 ዓመታት ያህል ያላባራው ለቅሷቸው፣ እዬዬአቸው ጭምር ነው። የኢትዮጵያ ሴቶችን ሁኔታ አኗኗር ስናስብ ከዓለም ሴቶች ሁሉ በተለየ እንድናየውና አምርረን እንድንታገል የሚያደርገን ከፊውዳላዊው የዘውድ አገዛዝ ይደርስባቸው ከነበረው የኢኮኖሚ ጥገኝነታቸውና የጾታ ጭቆና በተጨማሪ በፋሽስታዊው ደርግ አሁን ደግሞ በዘረኛው ወያኔ የአምባገነኖች አገዛዝ ዘመን የከፋና የባሰ በመሆኑ እጅግ ይቆጨናል።

የኢትዮጵያ እናቶች በደርግ ዘመን ልጆቻቸውን ቀይ ሽብር ቀስፎባቸዋል። ዛሬ ደግሞ በወያኔ ዘረኛና አምባገነን መንግሥት እናቶች ልጆቻቸውን በአሰቃቂ ሁኔታ አጥተዋል። ባህር በልቶባቸዋል፣ የበረሃ አሸዋ ውጦ አስቀርቶባቸዋል፣ የ"አጋዚ" ጥይት በለጋ እድሜያቸው ቀስፎባቸዋል፣ ይህ ነው ከሌላው ዓለም የጾታ ጭቆናና በደል በተጨማሪ እየደረሰባቸው ያለው መከራ። ስለሆነም የኢትዮጵያ ሴቶች ማርች 8ን ሲያስቡ የመብት ጥያቄ ብቻ አይደለም፣ ከወንድ እኩል አለመታየት ብቻ አይደለም፣ በጾታቸው ስለሚደርስባቸው በደልና ዝቅ ተደርገው ስለመታየታቸው ብቻ አይደለም፣ እውቀቱና ችሎታው እያላቸው ተገቢውን ቦታ ስለአለማግኘታቸው ብቻ አይደለም፣ ገጠር ውስጥ ዛሬም በኋላ ቀር አኗኗር ቀን ተሌት ስለምትማስነው ባተሌ ሴት ህይወት ብቻ አይደለም እጅግ---እጅግ ብዙ ብዙ

ዘርፈ ብዙ ችግሮች አሉ፤ መታየት መዳሰስ ያለባቸው የምንለው በዚህ እየደረሰ ባለው እውነት ላይ ተመርኩዘን ነው።

***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** የኢትዮጵያ ሴቶች ትግል ከመብትም አልፎ ትውልድ የማስቀጠልና የህልውና ጭምር ነው ብለን እናምናል። ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ሴቶችን ትግል ድርብ ድርብርብ እንዲሁም መራር የሚያደርገው።

ኢትዮጵያችን ዛሬ ማርች 8 ሲታሰብና ሲከበር የኢትዮጵያ እናቶችን ሁኔታ በተለየ ሁኔታ እንዲታይ የሚያደርገው፣ ዛሬ የኢትዮጵያ እናቶች ከጸታ ጭቆና ባሻገር በኢትዮጵያ ምድር ልጅ ወልዶ የማሳደግና በልጅ ወግ ማዕረግ የማየት ነገር ብርቅ ሆኖባቸዋል። የዛሬ 40 ዓመት በደርግና ተባባሪዎቻቸው ቀይ ሽብር ላጧቸው ልጆቻቸው እዬዬ ብለው ሳያለቅሱ ዛሬም በሌላ መልኩ ልጆቻቸውን ይነጠቃሉ። ያኔ ገና በመወለዳቸውና ዳዴ በማለታቸው የተረፉ ሕጻናት ዛሬ አድገው በ "አጋዚ" ጥይት ሲለቀሙ፤ ትላንት አልቅሳ ያባበቃች እናት ዛሬ በእስተርጅና የተጣበቀ አንጀቷን ይዛ እዬዬ ትላለች። ትላንት "ቀይ ሽብር ይፋፋም" እየተባለ የልጆቻቸው አስከሬን በራቸው ላይ የተጣለላቸው እናቶች፤ ዛሬ በወያኔ የ"አጋዚ" ጦር በቀሪ ልጆቻቸው ሬሳ ላይ ተቀምጠው እንዲጨፍሩና እንዲሳለቁ ተገደዋል። የኢትዮጵያ እናቶች ለአለፉት 50 ዓመታት ጧሪ ልጆቻቸውን ነው በተደጋጋሚ ያጡት። "ልጄ ለትምህርት ደረሰልኝ" የእኛ እናቶች ጋ ሲደርስ "ለሞት" ሆኗል።

ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን ማርች 8 ስንዘክር የእናቶች የግፍ ልቅሶ ውስጣችንን እያደማው፣ እያቆሰለው እንደሆን በመግለጽ ነው። ማርች 8ን ስንዘክር ይህንን በኢትዮጵያ እናቶች ላይ የደረሰውን መከራና ሰቆቃ ግንዝቤ ውስጥ በማስገባት መሆን አለበት። ማርች 8ንና የኢትዮጵያ እናቶችን ስናስብ ይህ ግፍ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ያሉ የዓለም ሴቶች ሁሉ እንዲያውቁትና ችግሩ እንዲወገድ አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ መሆን አለበት።

የካቲት ወር የአፍሪካውያን ሁሉ መኩሪያ የሆነው የአድዋ በዓል የሚከበርበት ነው። የአድዋ ድል የብልኋና የአስተዋይዋ የእቴጌ ጣይቱ የጦር አመራር ብቃትና ችሎታ ውጤት ጭምር እንደሆነ ታሪክ የሚያውቀው ሀቅ ነው። የአድዋን ገድል አጣጥመን በሳምንቱ ማርች 8ን ስናከብር ግን የምንዘክረው እንደ አድዋ ድል በታሪክ የወርቅ ቀለም የአሸበረቀውን ገድል አይደለም። የኢትዮጵያ ሴቶች ትግል ገና ብዙ መስዋእትነት የሚጠይቅ መሆኑን ግንዛቤ በመውሰድ ነው። ሴቶች በኢትዮጵያ ምድር በችሎታቸው፣ በብቃታቸውና በልምዳቸው ተፈላጊውን ቦታ እንዲያገኙ መታገል ገና ያልተነካ የቤት ሥራ መሆኑ መታወቅ አለበት። ከዚያ በፊት ግን እንባቸው መድረቅ ይኖርበታል። ግማሽ ምእተ ዓመት ሊሆን ጥቂት ለቀረው ጊዜ ያህል አልቅሰዋል። በዚህ ሀገር መውለዳቸውን እስኪረግሙ ድረስ ተሳቀዋል፤ ይህንን በደላቸውንና ግፋቸውን የማርች 8 ዓለም አቀፍ የሴቶች ማህበር አውቆት አብሮ ጩኸታቸውን ሊያስተጋባ ይገባል ለዚህም ***"አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ"*** ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል።

በዚህ አጋጣሚ የካቲት 23 ቀን 2010 ዓ.ም. በወያኔው የበላይነት በሚንቀሳቀሰው ኢሕአዴግ ምክር ቤት የፀደቀው ገዳይ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለሌላ ደም፣ ለሌላ ሕይወት በመንግስት ደረጃ የተዘጋጀ አጥፊ አዋጅ ነው። ይህ አዋጅ ወያኔ/ህወሓት የመጨረሻ የሞት ሽረት እስትንፋሱን የጅምላ ጭፍጨፋ በመላዋ ሀገሪቱ በማካሄድ "እኔ ከሞትኩ. . ." ሊተገብርብን የተነሳ ይመስላል። ይህ ድርጊት በርካታ ቤተሰቦችን፣ እናቶችን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ሀገራችንን በከፋ መልኩ ለማስለቀስ፣ እዬዬ ለማሰኘት የታቀደ የግድያ አዋጅ ተግባራዊ እንዳይሆን ሁሉም የኢትዮጵያ ልጆችና የፖለቲካ ድርጅቶች ከምንግዜውም በላይ በጋራ የምንተባበርበት ጉዳይ ነው። ልጆቻችንን ብቻ ለጥይት እየገበርን ማንባቱ ማብቃት ይኖርበታል። በዚህ የመጨረሻ ፍልሚያ እናቶችና አባቶች ቀዳሚውን ግዳጅ ለመወጣት ከልጆቻችን ጋር መሰለፍ ይኖርብናል።

**ዐድዋ፣ የአምስቱ ዓመት የፋሽስት ወረራ በድል የተቋጨው የእናቶች፣ አባቶች ከተዋጊው ሠራዊትና ከአርበኞቻችን ጋር እኩል ተሰልፈው ያበረከቱት አስተዋጽዎ እንደነበር ታሪክ በማህደሩ አስፍሮታል።**

**በመሆኑም ለ27 ዓመት በመንግሥትነት ልጅ እየፈጀ፣ እናቶችን እያስለቀሰ፣ አባቶችን እያስተከዘ፣ ሕፃናትን እያሳቀቀ የኖረው የወያኔ አገዛዝ ሊያበቃ የሚችለው ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል በእናት ሀገሩ ላይ የመጣ መቅሰፍትና በሕዝብ ላይ የመጣ የጥፋት ዘመን መሆኑን ተገንዝበን ይህንን አገዛዝ ለአንዴም ለመጨረሻ ለመቅበር ሁሉም ለትግሉ ግምባር ቀደም መሆን እንደሚገባው *“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ”* መልዕክታችንን በዚህ ማርች 8 ልዩ ዕትማችን እናሳስባለን።**

**ማርች 8 ለሴቶች እኩልነት! መብት! እና ነጻነት!**

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**

**እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ!**

**“አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ”**

**የካቲት 29 ቀን 2010 ዓ.ም. (March 08, 2018)**

**<u>ማሳሰቢያ ፡</u>**

- ውድ ወገኖቻችን ይህንን “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” «***ኢትዮጵያችን***» ዕትም በተለይ በሀገር ቤት ኮምፒዩተር የማግኘት ዕድል ለሌላቸው በማባዛት ታሰራጩት ዘንድ ቀና ትብብራችሁን በትህትና እንጠይቃለን።
- “አንድ ሀገር! አንድ ሕዝብ! ኢትዮጵያችን ሕዝባዊ ንቅናቄ” መስከረም 8 ቀን 2009 ዓ.ም. እራሱን ይፋ ያደረገ ሕዝባዊ ድርጅት ሲሆን የንቅናቄውን ማንፌስቶና ፕሮግራም www.ethiopiachen.org ከሚለው ድረ ገጻችን ማግኘት ትችላላችሁ።

ኢሜል ፡ ethiopiachen2009@gmail.com
info@ethiopiachen.org
ድረ ገጽ ፡ www.ethiopiachen.org
www.ethiopiachen.com

ምሥለ ገጽ ፡ 1H1H Ethiopiachen